ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንደሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ተስፋዬ ዘውዴ

ተጠሪ፡ ሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከንግድ ማህበር ክርክርን ጋር የተያያዘ ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/280896 ላይ ታህሳስ 15/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በፍርድ ቤቱ በተደረገ ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም የአሁን ተጠሪ በብር 4,000,000,000(አራት ቢሊዮን ብር) ካፒታል ግዙፍ የስኳር ፋብሪካ ለመገንባት ባወጣው የአክሲዮን ሽያጭ/ፕሮስፔክተስ/ ማስታወቂያ መሰረት የብር 200,000(ሁለት መቶ ሺህ ብር) አክሲዮን የአገልግሎት ክፍያ ብር 14,000(አስራ አራት ሺህ ብር) ጨምረው በመግዛት ከመስከረም 14/2005 ዓ.ም ጀምሮ በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ ባለአክሲዮን የሆኑ መሆኑን፣ ተጠሪ በአክሲዮን ማህበርነት ተቋቁሞ እና በንግድ ድርጅትነት ተመዝግቦ ስራ ለመጀመር የካፒታሉን ¼ኛ 1,000,000,000(አንድ ቢሊዮን ብር) ሰብስቦ በመቋቋም ላይ ባለው ማህበር ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ አድርጎ ይህንኑ በጋዜጣ ለህዝብ ማሳወቅ የሚገባው ሲሆን ተጠሪ ማህበር ግን በአጠቃላይ ከአባላቱ የሰበሰበው ከብር 100,000,000(አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) የማይበልጥ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ለተቋቋመበት ዓላማ በሚል ለኢንቨስትመንት ተብሎ ተሰጥቶት የነበረው መሬት በአስተዳደሩ የተወሰደበት መሆኑን፣ ከዚህም የተነሳ ማህበሩ መቋቋም እንዳልቻለ እና የተቋቋመበትን ዓላማም ማሳካት እንዳልቻለ ተገልፆ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ማህበሩ እንዲፈርስ መደረግ ሲገባው ከ11 ዓመታት በኋላ ተጠሪ ሓምሌ 05/2011 ዓ.ም በጠራው ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ ዓላማ ተለውጦ በግብርና ስራ እንዲሰማራ በአብላጫ ድምፅ የተወሰነ መሆኑን፣ በውሳኔው ያልተስማሙት 226 የማህበሩ አባላት ለአክሲዮን ግዢ የከፈሉት ገንዘብ ተከፍሏቸው ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ በዚሁ ውሳኔ ላይ የተገለፀ መሆኑን፣ አመልካች በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤው ላይ ያልተሳተፉ በመሆኑ

ውሳኔው ላልተቀበሉት አባላት የተጠበቀው መብት ተጠብቆላቸው ለአክሲዮን ግዢ እና ለአገልግሎት ክፍያ የከፈሉት ገንዘብ ከእነወለዱ ተከፍሏቸው ከማህበሩ ለመሰናበት ለተጠሪ ቢያሳውቁም ጥያቄው የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ የቀረበ አይደለም በሚል ውድቅ የተደረገ መሆኑን፣ ሆኖም የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ በጋዜጣ ያልወጣ በመሆኑ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው በመደበኛው የ10 ዓመት ይርጋ መሆን የሚገባው መሆኑን በመግለፅ ለአክሲዮን ግዢ እና ለአገልግሎት ክፍያ የከፈሉት ገንዘብ ክፍያውን ከፈፀሙበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ታስቦ በጠቅላላው ብር 386,373.25(ሶስት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ሶስት ከ25/100) ተከፍሏቸው ከአባልነት ለመሰናበት ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡ በአማራጭነት ደግሞ አክሲዮን ማህበሩ ላይ የመፍረስ አልያም የመክሰር ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚሉበትን ምክንያት በመጥቀስ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ ህዳር 16/2013 ዓ.ም የተፃፈ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርቦ መቃወሚያው በብይን ታላፏል፡፡ የሥረ ነገር ክርክሩ ይዘትም ማህበሩ በ30 መስራች አባላት ተቋቁሞ ከግንቦት 26/2001 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ መዝገብ የተመዘገበ በመሆኑ አመልካች ለህዝብ በወጣ የአክሲዮን ሽያጭ ማስታወቂያ መነሻነት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ አባል ሆነው እያለ ማህበሩ የካፒታሉን ¼ኛ መሰብሰብ አልቻለም በሚል ክስ ማቅረብ አይችሉም፣ አመልካች በማህበሩ አባልነት መቀጠል የማይፈልጉ ከሆነ የንግድ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ድርሻቸውን ሸጠው ከሚወጡ በቀር ማህበሩ ከተቋቋመ ከ11 ዓመት በኋላ ለአክሲዮን ግዢ እና ለአገልግሎት ክፍያ የተከፈለ ገንዘብ ከእነወለዱ እንዲከፈላቸው የሚጠይቁበት የህግ አግባብ የለም፣ በተጠቀሰው ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤውም የተወሰነው ማህበሩ ዋናውን የስኳር ምርት ስራ እስኪጀመር ድረስ ለጊዜው ጫካውን መንጥሮ ለአገዳ ሰብል በማዘጋጀት እና ተጓዳኝ የግብርና ምርቶችን በማምረት ለአስተዳደራዊ ወጪዎች መሸፈኛ የሚሆን ገቢ እንዲፈጥር የሚል እንጂ የማህበሩን መሰረታዊ ዓላማ የቀየረ አይደለም፣ ነው እንኳን ቢባል አመልካች በውሳኔው ካልተስማሙ ያላቸውን ድርሻ ሸጠው ከአባልነት መልቀቅ ይችላሉ የሚል እና ሌሎች ምክንያቶችን በመጥቀስ አመልካች በዋናነትም ሆነ በአማራጭነት የጠየቁት ዳኝነት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በተጠሪ ማህበር ላይ የመክሰር ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት የተጠየቀውን አማራጭ ዳኝነት ውድቅ በማድረግ በተቀሩት ሁለቱ የዳኝነት ጥያቄዎች ላይ አመልካች የጠየቁት ክፍያ ተከፍሏቸው ከማህበሩ አባልነት ሊሰናበቱ ይገባል? ወይስ አይገባም? እንዲሁም ተጠሪ ማህበር ሊፈርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን መርምሯል፡፡ በውጤቱም ተጠሪ ማህበር በ30 መሰራች አባለት ተመስርቶ ከግንቦት 2001 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ መዝገብ የተመዘገበ በመሆኑ ካፒታሉን ከህዝብ ለመሰብሰብ ለሽያጭ ያወጣው አክሲዮን ባለመሸጡ ምክንያት ማህበሩ አልተቋቋመም የሚባል አይደለም፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የተደረገውም ሐምሌ 05/2011 ሳይሆን ነሓሴ 05/2011 ነው፣ በጉባኤውም የተወሰነው በተጠሪ መመስረቻ ሰነድ ላይ በተመለከተው መሰረታዊ ዓላማ ላይ የጨመረ እንጂ ዓላማውን ለውጧል የሚያስብል አይደለም፣ አመልካች በማህበሩ አባልነት መቀጠል ካልፈለጉ ድርሻቸውን ሸጠው መውጣት ከሚችሉ በቀር የተጠቀሰውን ክፍያ ለመጠየቅ የሚያስችላቸው የህግ ምክንያት የለም በማለት ዋናውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጉዳይንም አስመልክቶ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም የኩባንያውን አስተዳዳሪዎች/የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት/ አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ማህበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ ሰጥቶ የማህበሩን ሂሳብ የሚያጣራ ሂሳብ አጣሪ ሾሟል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪ ማህበሩ እንዲፈር በሚል የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በትዕዛዝ ውድቅ የተደረገ ስለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

አመልካች መጋቢት 14/2014 ዓም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም በሁለት ዋና ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ ቀዳሚው የዳኝነት ጥያቄዬ ያለበቂ ምክንያት ከህግ አግባብ ውጪ ታልፎብኛል የሚል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ዋናው የዳኝነት ጥያቄዬ የሚታለፍበት ህጋዊ ምክንያት ሳይኖር በአማራጭ የዳኝነት ጥያቄው መነሻነት ኩባንያው እንዲፈርስ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

እነዚህኑ ነጥቦች አስመልክቶም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀዳሚውን የዳኝነት ጥያቄ ለማለፍ ሁለት ምክንያቶችን የጠቀሰ መሆኑን፤ የመጀመሪያው አክሲዮን ማህበሩ በህግ አግባብ የተቋቋመ በመሆኑ ከተቋቋመ ማህበር ለአክሲዮን መዋጮ እና ለአገልግሎት ክፍያ የተከፈለን ገንዘብ መልሶ የሚጠየቅበት አግባብ የለም የሚል መሆኑን፤ ሆኖም ፍርድ ቤቱ በዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የአክሲዮን ማህበር ምስረታ ሂደትን ከማህበሩ መቋቋም ሂደት ጋር ቀላቅሎ የተመለከተ መሆኑን፤ በንግድ ህጉ መሰረት አክሲዮን ማህበር ተቋቁሟል የሚባለው ጠቅላላ ባለአክሲዮኖች በመጀመሪያ በሚያደርጉት መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መሆኑን፤ ተጠሪ ማህበር ግን በዚህ መልኩ ያልተቋቋመ ሆኖ እያለ የማህበሩ መስራች አባላትን ጉባኤ እና የፈፀሙትን ክፍያ መሰረት አድርጎ ኩባኒያው እንደተቋቋመ መውሰዱ ከህግ አግባብ ውጭ መሆኑን፤ ኩባኒያው በንግድ ህጉ መሰረት ለመቋቋም በመመስረቻ ጽሁፉ ላይ ከተመለከተው አራት ቢሊዮን ብር ጠቅላላ ካፒታል ውስጥ ቢያንስ ¼ኛ ካፒታሉን መሰብሰብ የሚጠበቅበት ሲሆን የተሰበሰበው ግን ከ90 ሚሊዮን የማይበልጥ በመሆኑ በንግድ መዝገብ ያልተመዘገበ እና ሊመዘገብም የማይችል ሆኖ እያለ አክሲዮን ማህበሩ ተቋቁሟል መባሉ አግባብ እንዳልሆነ፤ በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ ላይ የተመለከተው የማህበሩ መሰረታዊ ዓላማ ስኳር ማምረት እንደሆነ፤ ኩባኒያው ይህንን ዓላማ ማሳካት ባለመቻሉ ነሓሴ 05/2011 በተደረገው ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይኸው መነሻ ተደርጎ በሌላ የሥራ ዘርፍ እንዲሰማራ፤ በዚህ የማይስማሙ አባላት ካሉ ድርሻቸው ተከፍሏቸው ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ በሚል ተወስኖ በዚሁ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የማህበሩ ዓላማ አልተለወጠም በሚል መነሻነት ቀዳሚው የዳኝነት ጥያቄው መታለፉ ከህግ አግባብ ውጭ ነው፤ ዋናው የዳኝነት ጥያቄዬ የሚታለፍበት ህጋዊ ምክንያት በሌለበትም በአማራጭ የዳኝነት ጥያቄው መነሻነት ማህበሩ እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ባቀረብኩት ዋናው የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍድር ቤት ያቀረቡት ዋናው የዳኝነት ጥያቄ የታለፈበት አግባብ በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ ነሓሴ 24/2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ኩባኒያው እንዲፈርስ በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ ተጠሪም የሚደግፈው መሆኑን፤ ከዚህ በመለስ ባለው ጉዳይ ተጠሪ ኩባኒያው በህግ አግባብ የተቋቋመ የንግድ ማህበር በመሆኑ አመልካች በማህበሩ አባልነት መቀጠል የማይፈልጉ ከሆነ ድርሻቸውን ሸጠው ከሚለቁ በቀር የአክሲዮን መዋጮ እና ሌሎች ክፍያ የሚጠይቁበት የህግ መሰረት የሌለ መሆኑን፤ ማብሩም መሰረታዊ ዓላማውን ያልለወጠ መሆኑን በመግልፅ ከዚህ አንፃር የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በበኩላቸው ባቀረቡት የመልስ መልስ ተጠሪ የማህበሩን መፍረስ በመቃወም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ሆኖ እያለ በራሱ የክርክር መስምር ጠይቆ ያጣውን ዳኝነት አመላካች ባስከፈተው መዝገብ ላይ ሊጠይቅ አይገባም የሚል እና ቀደም የቀረበውን የሰበር ቅሬታውን የሚያጠናክር ምክንያት በማከል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ በተያዘው ነጥብ ሳይወሰን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ክርክር በዋናነት የሚያጠነጥነው ተጠሪ አክሲዮን ማህበር በህግ አግባብ የተቋቋመ መሆን አለመሆኑ እና ማህበሩም መሰረታዊ ዓላማውን የለወጠ መሆን አለመሆኑ ዙሪያ ነው፡፡ እነዚህ ነጥቦች ደግሞ በአመዛኙ አግባብነት ባለው ማስረጃ ነጥረው መውጣት የሚገባቸው የፍሬ ነገር ክርክሮች ናቸው፡፡ እንግዲህ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ማረም እንጂ ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ችሎት ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን በግብዓትነት በመውሰድ ፍሬ ነገሩ መሰረት ተደርጎ በተሰጠ የህግ ትርጉም ውስጥ የተፈፀመ መሰረታዊ ስህተት ካለ ከመፈተሽ ባለፈ ማስረጃዉን በድጋሚ የሚመረምርበት እና የሚመዝንበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

ከዚህ አኳያ ተጠሪው አክሲዮን ማህበር በኩባንያ አመሰራረት ሂደት ማሟላት የሚገባውን መስፈርት አሟልቶ ከግንቦት 26/2001 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ሚኒስቴር ተመዝግቦ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የተባለውን ምስክር ወረቀት ተመልክቶ ማረጋገጡን በፍርድ ሀተታው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡ አንድ የአክሲዮን ኩባንያ የአመሰራረት ሂደት ሊከተለው የሚገባውን ሂደት እና መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በቀድሞ የንግድ ህግ ከቁጥር 312 እስከ 324፤ እንዲሁም በአዲሱ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 ከአንቀፅ 254 እስከ 265 በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡ በእነዚህ የአመሰራረት ሂደቶች ውስጥ የንግድ ማህበሩ በንግድ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ የአክሲዮን ማህበሩ አመሰራረት ሂደት የመጨረሻ ደረጃ ስለመሆኑ ከቀድሞ የንግድ ህግ ቁጥር 323 እና ከአዲሱ የንግድ ህግ አንቀፅ 265 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ አክሲዮን ኩባኒያ በዚህ መልኩ በንግድ መዝገብ ተመዝግቦ ህጋዊ ሰውነት ያገኘ ስለመሆኑ ስልጣን ባለው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ እያለ ማህበሩ አልተመሰረተም የሚለው ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ ይህ ችሎት አልተቀበለውም፡፡

ተጠሪ አክሲዮን ማህበር የተቋቋመበትን መሰረታዊ ዓላማ ለውጧል አልለወጠም የሚለውንም አስመልክቶ ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍርድ ቤት የኩባኒያውን መመስረቻ ጽሁፍ አስቀርቦ በመመርመር በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤው የተወሰነው ውሳኔ በመመስረቻ ጽሁፉ ላይ በነበረው መሰረታዊ ዓላማ ላይ ጭማሪ አድርጓል ከሚባል በቀር መሰረታዊ ዓላማውን ለውጧል የማያስብል ስለመሆኑ ማረጋገጡን የጠቀሰ በመሆኑ ከዚህ አኳያም የቀረበውን መከራከሪያ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

የማስቀረቢያ ነጥቡን በተመለከተ የአመልካች ቀዳሚ የዳኝነት ጥያቄ የነበረው ለአክሲዮን ግዢ እና ለአገልግሎት ክፍያ የከፈልኩት ገንዘብ ክፍያውን ከፈፀምኩበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ተከፍሎኝ ከማህበሩ አባልነት ልሰናበት ይገባል የሚል ነው፡፡ ለዚህ የዳኝነት ጥያቄ መነሻ ምክንያቱ

ደግሞ ተጠሪ ኩባንያ በህግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አግባብነት ያለውን የአመሰራረት ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ በንግድ ማህበርነት አልተመዘገበም የሚል ስለመሆኑ ከቀረበው ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለአክሲዮን ኩባኒያ ምስረታ ገንዘብ ያዋጡ ባለገንዘቦች እንዲህ ዓይነት መብት የሚኖራቸው ከባለአክሲዮኖች የተሰበሰበው ገንዘብ በምርስረታ ላይ ባለው ኩባኒያ ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ከተቀመጠበት ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ኩባንያው ሳይመሰረት በቀረበት ጊዜ ስለመሆኑ የቀድሞ የንግድ ህግ ቁጥር 312(3) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ባለፈ ህጋዊ ስርዓቱን ጠብቆ ከተቋቋመ የአክሲዮን ኩባንያ በዚህ መልኩ ክፍያ የሚጠየቅበት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡ እናም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ከዚህ አንፃር ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸው የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በቀዳሚነት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የሚታለፍ ከሆነ በሚል ተጠሪ ኩባኒያ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርስ ይገባል የሚሉበትን ምክንያት ጠቅሰው አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚሁ መነሻነት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳኛል ያለውን ማጣራት ካደረገ በኋላ በተጠሪ የአክሲዮን ማህበር ላይ የመፍረስ ውሳኔን አስተላልፏል፡፡ ይህ በአመልካች የዳኝነት ጥያቄ መሰረት የተከናወነ ነው፡፡ አመልካች ኩባኒያው እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቀው በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ መልሰው ይህንኑ የሚቃወሙበት የሙግት ሥነ ሥርዓት የለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ የመፍረስ ውሳኔን አስምልክቶ የአሁን ተጠሪ በሌላ የክርክር መስመር እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁ/217866 ላይ ታህሳስ 14/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በሚል የፀና በመሆኑ በዚህ መዝገብ ላይ በቀረበው ቅሬታ መነሻነት የመፍረስ ውሳኔው ተመርምሮ የተለየ አቋም የሚያዝበት ስርዓት የለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ካቀረቡ የሰበር አቤቱታ አንፃር በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ሊያስብል የሚችል ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/280896 ላይ ታህሳስ 15/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

Daniel Fikadu Law Office

ዳንኤል ፍቃዱ ጠበቃና የህግ አማካሪ